---

بسم الله الرحمن الرحيم

# በኢትዮጵያ ተደጋግመው በተከሰቱ፤ በተለይም በቅርቡ አክራሪና ጽንፈኛ ክርስትያኖች በሙስሊሞች ላይ ያደረጉትን ትንኮሳ ተከትሎ በሀገሪቱ ዉስጥ እየተባባሰ የመጣዉን ውጥረት በተመመለከተ ከአውሮፓ የኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች ኔትዎርክ የተሰጠ የአቋም መግለጫ

## ኢትዮጵያ የሁሉም ዜጎቿ ሀገር ናት!

ኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች በተለያዩ ጊዜያት በሀገሪቱ በተከሰቱ መንግስታትና ስርዓቶች በሀገራቸው እንደ ባዕድ ሲታዩና "በኢትዮጵያ የሚገኙ እስላሞች" እየተባለ እንደ ሁለተኛ ዜጋ ሲቆጠሩ፤ የዜግነትና የሰብዓዊ መብቶቻቸውን ተነፍገው ለስቃይና መከራ ተዳርገው እንደነበር ዘወትር የምናስታውሰው ነው፡፡

ከፊውዳሉ ስርዓት መውደቅ ጀምሮ በሀይማኖቶች መካከል የነበሩ አድሏዊ ግኑኝነቶች መቀነሳቸው ባይካድም ሙሉ ለሙሉ ግን አልተቀረፉም፡፡ የኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች የመብትና የእኩልነት ጥያቄዎችም  እስካሁን የሚጠብቁትን ያክል ምላሽ አላገኙም፡፡ በተለይም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በሙስሊሙ ህብረተሰብ ላይ እየተፈጸሙ ያሉት ችግሮች  እነዚህን የመብትና የእኩልነት ጥያቄዎቹን አሳሳቢ አድርገዋቸዋል፡፡

ኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች በሀገራቸው ዉስጥ ከሀይማኖታቸው ጋር በቀጥታ ግንኙነት ባለው መልኩ የሚደርሱባቸው በደሎች በርካታ ናቸው፡፡ ከነዚህም ዉስጥ አንዳንዶቹን ለመጥቀስ፡- የሙስሊሙ መንፈሳዊ መጽሃፍ የሆነዉን ቅዱስ ቁርዓንን ቀዳዶ ለመጸዳጃነት ከመጠቀም ጀምሮ  ወጣት ሙስሊም ተማሪዎች ከዕምነታቸው ጋር በተገናኘ ሁኔታ ከትምህርት እንዲደናቀፉ የሚያደርጉ እርምጃዎች ተወስደዋል። በአክሱም የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች እስካሁን ድረስ የፀሎት ቦታ እንዳይኖራቸው መደረጉ ብቻ ሳይሆን ጥያቄውን ማቅረቡ በራሱ እንደወንጀል መታየቱ አሁንም እንደቀጠለ ይገኛል። ሙስሊሙን በገዛ ሀገሩ የባይተዋርነት ስሜት እንዲሰማው የሚያደርጉ አገላለጾችና ድርጊቶች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተበራከቱ መጥተዋል። "ኢትዮጵያ የክርስትያን ደሴት ናት"፣ "የአባቴን እርስት አሳልፌ አልሰጥህም"፣ "ሙስሊሞች ከኢትዮጵያ ዉጡ - ለ1400 አመት አስተናገድናችሁ" ወ.ዘ.ተ የሚሉ መፈክሮች በከናቴራዎችና በፖስተሮች ላይ እየታተሙ በሰፊው ተሰራጭተዋል፡፡ የሙስሊሙን ሞራልና ክብር የሚነኩና እምነቱንም የሚያንቋሽሹ ዲስኩሮች (ሰበካዎች) በአደባባይ ሳይቀር ይደረጋሉ።  ፀረ-ኢስላምና ፀረ-ሙስሊም ጽሁፎች ያለምንም ገደብ በየጊዜው እየታተሙና እየተበተኑ ይገኛሉ። እነዚህ ሁሉ እንግዲህ በሀገራችን የሃይማኖት ግጭቶች እንዲከሰቱ መንስዔ ከመሆን አልፈው የሀገሪቱን አጠቃላይ ሰላምና የዜጎቿን ተከባብሮ አብሮ የመኖርን ዘይቤ አሳሳቢ ደረጃ ላይ አድርሰውታል፡፡

በሀገራችን ዉስጥ የሚታየው ሃይማኖታዊ ግጭት አፋጣኝ መፍትሄ ሳያገኝ ቀርቶ ከከረረ ደረጃ ላይ ከደረሰ በቀላሉ ልንፈታው ከማንችለው ችግር ዉስጥ እንዳንገባ የሚያሰጋን ነው። ውይይት የሚያሻዉን በዉይይት፤ ህጋዊ መፍትሄ የሚያሻዉን ደግሞ ፍትሃዊነት በተሞላበት ዳኝነት እልባት ካልተደረገለት ዛሬ ትኩረት ሳንቸረው አድበስብሰን ያለፍነው ነገ ህዝባችንን በዘር፣ በጾታ፤ በእድሜና  በሃይማኖት ሳይለይ ለጥፋት የሚዳርግ መሆኑን መዘንጋት የለብንም። ሂደቱ ካልተገታ የሃገራችንን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ኑሮ ከማዳከም አልፎ  ከጉዳዩ ዓለማቀፋዊ ይዘት በመነሳት የሌሎች ሃገሮችም ጣልቃ እንዲገቡበት የሚጋብዝ ነው።

መንግስት ያለበትን ሃላፊነቱን ተረድቶ በክርስትና እምነት ጀርባ የተሰከሰኩ ጽንፈኞችና አክራሪዎች በሙስሊሙ ህብረተሰብ እምነት፣ ማንነትና ንብረት ላይ እያደረሱ ላላው ጥቃት፣ ሺብርና የሙብት ገፈፋ ህጋዊ መፍትሄ ይሰጣል የሚል እምነት ነበረን። የሃይማኖት አባቶችና ተቋማት በተለይም ቤተክህነት ጉዳዩን ሳትሸፋፍን ለሀገርና ወገን ደህንነት፤ በሰላምም አብሮ ለመኖር ስትል ድርጊቱን አዉግዛ በእቅፏ ያሉ አክራሪዎችና ጽንፈኞችን አጋልጣ ከሙስሊሙ ህብረተሰብ  ተወካዮች ጋር በዉይይት፣ በመቻቻልና በመከባበር አብሮ ለመኖር የሚጋብዝ እርምጃን ትወስዳለች የሚል እምነትም ይዘን ጉዳዩን ጊዜ ሰጠተን ተከታትለናል። ሆኖም ግን እስካሁን ይህ አደገኛ ጉዳይ የሚገባውን ትኩረት አገኝቶ፤ የሚመለከታቸው ክፍሎችም ሃላፊነታቸውን ለመወጣት ይህ ነው የሚባል እርምጃን ለመውሰድ ተዘጋጂተው አላየንም። ይባስ ብሎ በከፍተኛ እርከን ላይ የተቀመጡ “የሀይማኖት አባትና ምሁር” ተብየዎች ሳይቀሩ አክራሪዎቹ ላደርጉት ተግባርና ትንኮሳ ሽፋን ሊያደርጉላቸው ሲጥሩ እያስተዋልን ነው። በመሆኑም በአውሮፓ የኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች ኔትዎርክ የሁሉም ሃይማኖቶች መብቶች በእኩልነት እንዲከበሩ፣ ዜጎች እኩል የሆነ መብቶች እንዲኖራቸው፤ ሃይማኖቶች ተከባብረዉ በጋራ ለሀገራቸው ግንባታና ለተሻለ ኑሮ እንዲሰሩ፤ የዜጎች ሰላማዊ ግንኙነት ይበልጥ እንዲዳብር ያለውን ፅኑ ፍላጎና ምኞት ለመግለጽ፤ አሁን የተከሰቱትም ሆኑ ወደፊት የሚፈጠሩ ችግሮች በጋራ በዉይይት መፈታት እንደሚገባቸው ለማስገንዘብ፤ ፍትህና እኩልነት ሰፍኖ በሰላም አብሮ ለመኖር አስፈላጊ ናቸው ብሎ ያመነባቸዉን ጉዳዮች ለማመላከት ይህን መግለጫ አውጥቷል፡፡ በዚህም መሰረት፡-

1. ከየትኛውም ሀይማኖት በፊት ኢትዮጵያ ነበረች፡፡ ሃይማኖቶች ወደሃገራችን ሲገቡ የጊዜ ቅደም ተከተል ያላቸው መሆኑ ሲታወቅ ኢትዮጵያን የአንድ ሃይማኖት ባለቤት አድርጎ መውሰድ ግን ስህተት ከመሆኑም አልፎ አደገኛ ነው። ህዝባችን ተከባብሮና ተፋቅሮ በአንድነት እንዳይኖር በሃይማኖት ሽፋን ህብረተሰቡን በመከፋፈል ብጥብጥ ዉስጥ እንዲገባ የሚያደርጉ፤ በዚህም እኩይና የፀብ አጫሪነት ተግባራቸው ሀገራችንን ሰላም ለመንፈግ የሚጥሩ ሃይሎች በሁሉም የህብረተሰብ ክፍል እንዲወገዙና እንዳስፈላጊነቱም በህግ ፊት ቀርበው አግባብ ያለው ፍርድ እንዲሰጣቸው፡፡

2. ሙስሊሙ ህብረተሰብ ማንም ጣልቃ ሳይገባበት የመደራጀት፣ የመማር፣ የመስራት፣ በሰላም እምነቱን የማራመድና የመግለጽ ነጻነቶች በዜግነቱ ሊያገኛቸው የሚገቡ በመሆናቸው እነዚህ መብቶቹን በሃይማኖታዊ ማንነቱ ሳቢያ መሸራረፍ እንዲቆም፤ አድሎዓዊ አሰራሮችም እንዲወገዱ።

3. ዜጎች የሃይማኖት ልዩነት ሳያግዳቸው በሰላም በመከባበርና በመፈቃቀር አብረው መኖር ይችሉ ዘንድ፤ የህዝቡን ሀገራዊ አንድነትና ህብረቱን ለማጠናከርም ይቻል ዘንድ በሀገሪቱ ህገ-መንግስት የተረጋገጠው የዜጎችና የሃይማኖቶች ነጻነትና እኩልነት ተፈጻሚ እንዲሆን፡፡

4. ኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች የሃገሪቱን ህገ-መንግስት ባከበረና የሌሎችን መብት ባልተጋፋ መንገድ ሌሎች ለዘመናት በብቸኝነት ሲጠቀሙባቸው በኖሩት በህትመትም ሆነ ተመሳሳይ መንገዶች ሃይማኖታቸዉን ለማስተማር የሚያደርጉትን ጥረት በጥላቻና በስጋት ከሚያዩ አክራሪና ጽንፈኞች በኩል ለሚደርስባቸው ጥቃት ህጋዊ ጥበቃ እንዲደረግላቸው፡፡

5. ማንኛዉም የሀገሪቱ ዜጋ በፍላጎቱና በምርጫቸው የሚከተለው ኃይማኖታዊ እምነቱ ተከብሮለት ከሌላ እምነት ተከታይ ወገኖቹ ጋር ተቻችሎ የሚኖርበት ሁኔታ እንዲበረታታ።

6. የመንግስትም ሆኑ የግል የዜና አውታሮች በሙስሊሞችና እምነታቸውን ላይ የሚያደርጉትን ትችትና የስነ-ልቦና ጥቃት እንዲያቆሙ፤ ከሀይማኖታዊ አድሏዊነት ነጻ የሆነ ግልጋሎት ለህዝባቸው እንዲሰጡ። የአንድን እምነት ብቻ የበላይነት በስፋት ከማንጸባረቅ ተቆጥበው በአገሪቱ ዉስጥ ያሉ ሃይማኖቶች በእኩልነት መብታቸው የሚከበርበት ሁኔታ እንዲፈጠር አስተዋጽዎ እንዲያደርጉ፡፡

7. በተለያዩ እርከኖች ላይ የሚገኙ የሙስሊሙ ህብረተሰብ መሪዎች ለችግሩን መፍትሄ ለማፈላለግ የሚያስችሉ የውይይት መድረኮችን አዘጋጂተው ሰፊውን ህብረተሰብ በጉዳዩ ላይ እንዲያወያዩ፤ የሙስሊሙን ፍላጎትም አግባብ ባለው መልክ ግልጽ እንዲያደጉ። ኢትዮጵያዊያን በዘር፣ በጎሳ፣ በባህል፣ በቋንቋ እንዲሁም በሀይማኖት ሳቢያ ያሏቸውን ልዩነቶች አቻችለው አብረው መኖር ይችሉ ዘንድ እንደዚሁም ለጋራ ጥቅም ለሀገር ሰላምና እድገት ሙስሊሙ ትዕግስት በተሞላበት ሁኔታ ተግቶ እንዲሰራ፡፡ በዚህ ሂደትም የፖለቲካም ሆነ ልዩ ጥቅምና አላማ ላላቸው አካላት መሳሪያ ከመሆን እንዲጠነቀቅ።

8. ሙስሊሙ ህብረተሰብ በኢትዮጵያ ፖለቲካዊ መድረኮች ላይ የሚነሱ የሀገር ጉዳዮችን ችላ ሳይልና ራሱን ሳያገል፤ ህጋዊ አግባብነት ባለው መልኩ ራሱን አደራጅቶ ለሀገሩ ህልዉና፣ ለህዝቦቿ መብት መከበር፣ ለሰላሟ መጠበቅ፣ ለእድገቷና ብልጽግናዋ መፋጠን ሃላፊነት ያለበት በመሆኑ በመጭው አገር አቀፍ ምርጫ ላይ የመምረጥና የመመረጥ መብቱን በአግባቡ ለመጠቀም ከአሁኑ እንዲንቀሳቀስ።

በመጨረሻም በተለይ መንግስት ይህን ጉዳይ ትኩረት ሰጥቶ ሊከታተለውና አግባብ ያለው እርምጃም መውሰድ የሚጠበቅበት መሆኑን በድጋሜ እያሳሰብን፤ የሲቪክ ማህበረሰቡ፣ የሃይማኖት አባቶችና ተቋማት፣ የፖለቲካ ድርጂቶች፣ የመገናኛ ብዙሃን፣ ለሰብዓዊ መብት መከበር ቆመናል የሚሉ አካላት፤ እንዲሁም ማንኛዉም የኢትዮጵያ ደህንነትና ሰላም ያሳስበኛል የሚል ሁሉ ይህ በሀገራችን እየተባባሰ የመጣዉ የሃይማኖቶች ግጭት እንዲቆምና ያለው ዉጥረት እንዲረግብ የማድረግ ሃላፊነት እንዳለበት እያስገነዘብን፤ ኔትወርካችን እንደ ድርጂት አባሎቹም እንደግለሰብ የሚጠበቅባቸውን ሁሉ ለማድረግ ዝግጁ መሆናቸውን ጨምረን እንገልጻለን።

ሰላም ለሃገራችንና ለህዝባችን እንመኛለን! ይህም በሁሉም ልጆቿ ጥረት፣ በአላህ እገዛና ፍቃድ እውን ይሆናል።

ኢትዮጵያ የሁሉም ዜጉቿ ሀገር ነች።

በአዉሮፓ የኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች ኔትዎርክ
ስቶክሆልም - ስዊድን
ማርች 09፣ 2009